# 5ኛ ትምህርት

*ጥቅምት 12-18 2009 ዓ.ም* *October 22— 28*

## ቀኑ የተረገመ ይሁን

ሰንበት ከሰዓት

**ለዚህ ሳምንት ጥናት የሚከተሉትን ጥቅሶች ያንብቡ፡-** ኢዮብ 3፡1-10፣ ዮሐንስ 11፡11- 14፣ ኢዮብ 6፡1-3፣ 7፡1-11፣ ያዕቆብ 4፡14፣ ኢዮብ 7፡17-21፣ መዝ. 8፡4-6፡፡

**መታሰቢያ ጥቅስ፡-** "ጌታችንና አምላካችን ሆይ፣ አንተ ሁሉንፈጥረሃልና ስለ ፈቃድህም ሆነዋልና ተፈጥረውማልና ክብር ውዳሴ ኃይልም ልትቀበል ይገባሃል፡፡" ራዕይ 4፡11

የ ኢዮብን መጽሐፍ ስናነብ ሁለት ጥቅሞችን እናገኛለን፡- የመጀመሪያው እንዴት እንደሚያልቅ ማወቃችን ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ስለማይታየው ታላቁ ተጋድሎ ውስጣዊ መንስኤ ማወቃችን ነው፡፡

ኢዮብ እነዚህን ነገሮች አያውቅም ነበር፡፡ የሚያውቀው ህይወቱ በመልካም ጎዳና እየተጓዘ በነበረበት ወቅት ብዙ ችግሮችና ውጣውረዶች በእርሱ ላይ እንደመጡ ብቻ ነው፡፡ ሲቀጥል "በምስራቅ ካሉት ሰዎች ሁሉ ይልቅ ታላቅ" (ኢዮብ 1፡3) የተባለው ሰው በአመድ ላይ ተቀምጦ ወደ ማልቀስና መጮህ ደረጃ ሲወርድ እንመለከታለን፡፡ የኢዮብን መጽሐፍ ማጥናታችንን ስንቀጥል ግራ መጋባቱን፣ ንዴቱንና ለቅሶውን እናስተውል ዘንድ በኢዮብ ቦታ ራሳችንን ለማስቀመጥ እንሞክር፡፡ በአንድ መልኩ ይህ እጅግ ሊከብደን አይገባም አይደል? ኢየብ የደረሰበትን ያክል ደርሶብናል ማለት ሳይሆን ከኛ መካከል በዚህ በወደቀ ዓለም ከስጋ ተወልዶ በተለይም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ማድረግ ሲፈልግ ብዙ ስቃይና ውስብስብ መከራን ያልተጋፈጠ ማን አለ?

**የዚህን ሳምንት ትምህርት አጥንተው ለጥቅምት 19 ሰንበት ይዘጋጁ፡፡**

## ቀኑ ይጥፋ

ራስዎን ኢዮብ እንደሆኑ ያስቡ። ሊገልፁት በማይችሉት መልኩ እርስዎ የሰሩት ነገር፣ የተከናወኑልዎት፣ ጌታ በባርኮቱ የጎበኝዎት ነገሮች በሙሉ ፈራርሰው ጠፉ። ግራ የሚያጋባ ነገር ነው። ለተፈጠረው ነገር ምንም መልካምም ሆነ መጥፎ መንስኤዎችን አናውቅም።

ከዓመታት በፊት የህጻናት ተማሪዎች ሰርቪስ አውቶቢስ መንገዱን ስቶ ብዙ ህፃናት ሞቱ። በዚያ አውድ አንድ እግዚአብሔር የለም ባይ "ትርጉም፣ አላማና አቅጣጫ በሌለው አለም ላይ የሚጠበቀው እንደዚህ አይነት ክስተት ነው።" ብሎ ተናግሯል። እንደ እርሱ አባባል ህይወት ራሱ ትርጉም አልባ ስለሆነ እንደዚያ አይነት አሳዛኝ ክስተትም ትርጉም የለሽ ነው።

ቀደም ብለን እንዳየነው ይህ መልስ በእግዚአብሔር ለሚያምነው ሰው አይሰራም። የጌታ ታማኝ ተከታይ ለሆነው ኢዮብም ይህ መልስ አይሰራም። ታድያ መልሱ ምንድነው? እንዴት ነው የምናብራራው? ኢዮብ መልስ አልነበረውም። ያለው መከራውና በዙሪያው ያሉት ያልተመለሱ ጥያቄዎች ናቸው።

**ኢዮብ 3:1-10ን ያንብቡ። ኢዮብ በመጀመሪያ ሃዘኑን የገለጠው እንዴት ነው? እያለ ያለው ነገር ከኛ ሁኔታ ጋር በምን ይገናኛል?**

---

---

ህይወት በእርግጥም የእግዚአብሔር ስጦታ ነው። የምንኖረው እግዚአብሔር ስለፈጠረን ብቻ ነው። (ሐዋ. 17:28፣ ራዕይ 4:11) መኖር መቻላችን እራሱ ዘመናዊውን ሳይንስ ያስደመመ ተዓምር ነው። በእርግጥም ሳይንቲስቶች በህይወት ትርጉም፣ እንዴት እና ለምን እንደመጣን በተመለከተ አንድ ወጥ አቋም የላቸውም።

ታድያ በመከራ ጊዜያት መኖርን ያልጠላ ማን አለ? እያወራን ያለነው ደስ ስለማይሉ ራስ የማጥፋት

ሙከራዎች አይደለም። ከዚያ በላይ ልክ እንደ ኢዮብ መጀመሪያውኑ ባልተወለድን ብለን ስለተመኘንባቸው ቀኖችስ?

አንድ የጥንት ግሪካዊ እንደተናገረው "ከመሞት ሌላ በአንድ ሰው ላይ ሊሆን የሚችለው ምርጡ ነገር መጀመሪያውኑም አለመወለድ ነው።" ህይወት እጅግ በመከራ ከመሞላቷ የተነሳ ሳንፈጥር ቀርተን በዚህች በወደቀችው ዓለም የሰው ህይወት የሚያጋጥመውን አይቀሬ ምሬት ሳንቀምስ ብንቀር የተሻለ የሚሆንበት ጊዜ አለ።

**ኢዮብ እንደተሰማው ባልተወለድኩ ብለው አስበው ያውቃሉ? ታድያ ምን ተፈጠረ? መቼም የተሻለ ስሜት አሁን እየተሰማዎት ነው። እጅግ በከፋው የህይወታችን ጊዜ እንኳን ነገሮች እንደሚሻሻሉ ተስፋ ማድረግ የሚጠቅመን ለምንድነው?**

*ሰኞ ጥቅምት 14* *October 23*

## በመቃብር ባረፍኩ

**ኢዮብ 3፡11-26ን ያንብቡ። ኢዮብ በዚህ ቦታ እየተናገረ ያለው ምንድ ነው? ለቅሶውን እየቀጠለ ያለው በምን መልኩ ነው?**

____________________________________________________________

____________________________________________________________

ምስኪኑ ኢዮብ ያጋጠመውን መራራ ኃዘን በምናባችን እንሳለው። ንብረቱ መጥፋቱ፣ ጤናውን ማጣቱ ሳያንስ ሁሉንም ልጆቹን ማጣቱ እጅግ ከባድ ነገር ነው። አንድ ልጅን ማጣት እንኳን ምን ያክል ከባድ እንደሆነ ይታወቃል። ኢዮብ ግን አስሩንም ልጆቹን አጣ። ኢዮብ ሞትን መመኘቱ አይገርምም።

**ደግሞም ኢዮብ በምን ምክንያት ይህ እየሆነ እንዳለ አላወቀም፤ ቢያውቅ የተሻለ ስሜት ይሰማው ይሆን?**

ኢዮብ ስለሞት የተናገረውን ልብ ይበሉ። ቢሞት ኖሮስ ከዚያ ምን ይሆናል? ሰማይ ይገባል? እግዚአብሔር ባለበት ከመላዕክቱ ጋር በገና እየደረደረ ይዘምራል? እዚህ ቦታ ላይ እንደዚያ አይነት አስተምህሮ አላስተማረም። በተቃራኒው ኢዮብ ምን አለ? "አሁን ተኝቼ ዝም ባልሁ ነበር፤ አንቀላፍቼ ባረፍሁ ነበር። " (ኢዮብ 3፡13)

**መክብብ 9:5ንና ዮሐንስ 11:11-14ን ያንብቡ። ኢዮብ የተናገረው ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ካስተማረው ጋር እንዴት አብሮ ይሄዳል?**

---

ከቀደምቶቹ የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፎች አንዱ የሆነው ይህ መጽሐፍ አስቀድሞ ስለ "ሙታን ሁኔታ" ተናገረ። በዚህ ሰዓት ኢዮብ የፈለገው "ማረፍን" ነበር። ህይወት በድንገት እጅግ የስቃይ ሆናበት ሞቱን ናፈቀ፤ በመቃብር በሰላም ማረፍን ተመኘ። እጅግ ከማዘኑና ከመጎዳቱ የተነሳ ችግሩ ከመምጣቱ በፊት የነበረውን ደስታ ረስቶ ገና ስወለድ በሞትኩ ብሎ ተመኘ።

**እንደ ክርስትያኖች ለወደፊቱ ምርጥ ተስፋዎች አሉን። በተመሳሳይ ሁኔታ ደግሞ አሁን ካለው መከራ ባሻገር ከዚህ በፊት ያጋጠሙንን መልካም ነገሮች አስታውሰን ከዚያ መፅናናትን ማግኘት የምንችለው እንዴት ነው?**

## የሌሎች ህመም

ኢዮብ በምዕራፍ 3 ላይ የተቀመጠውን የመጀመሪያውን የሰቆቃ ቃል ጨረሰ፡፡ በቀጣዮቹ ሁለት ምዕራፎች ከጓደኞቹ አንዱ የሆነው ኤሊፋዝ ለኢዮብ ትምህርት ይሰጠዋል (በሚቀጥለው ሳምንት ይህንን እንመለከተዋለን) ፡፡ በምዕራፍ 6ና 7 ስለ ስቃዩ መናገሩን ይቀጥላል፡፡

**"ትካዜዬ ምነው በተመዘነ ኖሮ! መከራዬም ሁሉ ምነው በሚዛን ላይ በተደረገ ኖሮ! ከባህር አሸዋ ይልቅ ይከብድ ነበርና፡፡" (ኢዮብ 6፡2-3) ኢዮብ ህመሙን እየገለፀ ያለው እንዴት ነው?**

---

ይህ ምስል ኢዮብ መከራውን በምን መልኩ እየተመለከተው እንደሆነ ፍንጭ ይሰጠናል፡፡ የባህር ሁሉ አሸዋ በአንዱ ሚዛን ላይ ቢሆንና "ትካዜውና መከራው" ደግሞ በሌላ ሚዛን ቢቀመጥ መከራዎቹ ከአሸዋዎቹ በልጠው ይመዝኑ ነበር፡፡ ለኢዮብ መከራው ይህን ያክል ከባድ ነበር፡፡ ይህ ደግሞ የሌላ የማንም ሳይሆን

የኢዮብ መከራ ብቻ ነበር፡፡ አንዳንድ ጊዜ "የሰብአዊ ዘር መከራ" የሚልን ኃሳብ እንሰማለን፡፡ ሆኖም ይህ እውነታን አይገልጽም፡፡ በማህበር አንሰቃይም፤ የማንንም ስቃይ ሳይሆን የራሳችንን ስቃይ ነው የምንሰቃየው፡፡ የምናውቀው የራሳችንን ህመም የራሳችንን ስቃይ ብቻ ነው፡፡ የኢዮብ ስቃይ ምንም እንኳን ታላቅ ቢሆንም ማናችንም ልናውቀው ከምንችለው በላይ የሆነ ስቃይ አልነበረም፡፡ አንዳንድ ሰዎች ሌላውን ሰው "ስቃይህ ይገባኛል" ሊለው ይችላል፡፡ አይሰማቸውም፤ ሊሰማቸውም አይችልም፡፡ የሚሰማቸው በሌላ ሰው ስቃይ ምክንያት የሚሰማቸው ህመም ብቻ ነው፡፡ ያ ግን የሌሎች ሰዎች ህመም ሳይሆን የነርሱ ስሜት ብቻ ነው፡፡

የተለያዩ ሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ብዙ ሰዎችን ለሞት ሲዳርጉ ሰምተናል፡፡ የሞቱትና የተጎዱት ሰዎች ቁጥር ያስገርመናል፡፡ ያን ሁሉ ከፍተኛ ስቃይ በምናባችን መሳል ይከብደናል፡፡

ልክ እንደኢዮብ እንዲሁም ከአዳምና ሄዋን ጀምሮ በውድቀት ውስጥ እንዳለው ሰብዓዊ ዘር ሁሉ እያንዳንዱ ሰው የራሱን ስቃይ (ህመም) እንጂ የሌላውን ሊያውቅ አይችልም፡፡

በእርግጥ መቼም ቢሆን የሰዎችን ስቃይ ማቃለል አንፈልግም፤ ደግሞም እንደ ክርስትያንነታችን የተጠራነው በምንችለው ሁሉ ለተቸገሩት ለመድረስ ነው (ያዕቆብ 1:27፣ ማቴ. 25:34-40) ፡፡ ሆኖም በዓለም ላይ ምንም ያክል ስቃይ ቢኖር የትኛውም ሰብዓዊ ዘር (ከአንዱ በቀር፣ 12ኛ ትምህርትን ይመልከቱ) አንድ ሰው ሊሰማው ከሚችለው በላይ ስላልተሰቃየ ልናመሰግን ይገባናል፡፡

**የሰብአዊ ዘር ስቃይ በእያንዳንዱ ሰው ልክ የመሆኑ ኃሳብ ላይ ጊዜ ወስደው ያሰላስሉ፡፡ ይህ አስቸጋሪውን የሰው ልጅ ስቃይ በተለየ መልኩ እንዲያዩት የሚረዳዎት እንዴት ነው?**

*ረቡዕ ጥቅምት 16* *October 24*

## የሽማኔው መወርወሪያ

ቀጣዩን ንግግር በምናብዎ ይሳሉ፡፡ ሁለት ሰዎች በሰብዓዊ ዘር ሁሉ ዕጣ ፈንታ በሆነው ሞት ዙሪያ በግርምት እየተነጋገሩ ነው፡፡ ያም ሰዎች ህይወታቸው ምንም ያህል መልካም ቢሆን ምንም ያህል ስኬታማ ቢሆኑ የሚጠናቀቀው በሞት ነው፡፡

"አዎን" አለ ማቱሳላ ለጓደኛው፡- "አንድ 800፣ 900 ዓመታት ኖረን ከዚያ እንሞታለን፡፡ 800 ወይም 900 ዓመት ዘላለም ከመኖር አንፃር ምንድናት?" (ዘፍጥረት 5)

ለብዙ መቶ አመታት መኖርን ማሰብ ለኛ ከባድ ቢሆንም (ማቱሳላ ልጁ ላሜህ ሲወለድ 187 አመቱ ነበር፤ ከዚያ በኂላ ለ782 ዓመታት ኖሯል) ጥንታዊዎቹ ሰዎች እንኳን የሞትን እውነታነት ሲጋፈጡ የህይወት አጭር መሆን ያሳዝናቸው ይሆናል፡፡

**ኢዮብ 7:1-11ን ያንብቡ፡፡ የኢዮብ ቅሬታ ምንድነው? መዝ. 39:5፣11ንና ያዕቆብ 4:14ን ይመልከቱ፡፡**

ኢዮብ ከሞት የሚመጣውን ዕረፍት ሲመኝ ተመልክተነዋል። አሁን ደግሞ ህይወት ወዲያው እንደምታልፍ እያሰበ ያለቅሳል። እያለ ያለው ህይወት ከባድ፣ በመከራና በስቃይ የተሞላች ትሆንና ከዚያ እንሞታለን ነው። ህይወታችን በስቃይና በሀዘን የተሞላ ሆኖ እንኳን ስለ ህይወት አጭርነት ማጉረምረማችን እንቆቅልሽ ነው።

አንዲት ሰባተኛ ቀን አድቬንቲስት ሴት በአእምሮ መጨናነቅ (ዲፕሬሽን) ምክንያት ራስን ለመግደል እስከመሞከር ድረስ የተሰቃየችውን ስቃይ በጽሁፍ አስፍራው ነበር። ሆኖም "ከመደበኛው ዕድሜ ተጨማሪ ስድስት ዓመት መኖር የሚያስችል የአኗኗር ዘይቤ የምከተል አድቬንቲስት መሆኔ ሁኔታውን የበለጠ የከፋ ያደርገዋል።" ብላ ፅፋለች። ይህ ትርጉም አይሰጥም። በእርግጥም በህመምና በስቃይ ጊዜያት ብዙ ነገሮች ትርጉም የሚሰጡ አይመስሉም። አንዳንዴ አመዛዝነን ማሰብ አቅቶን የሚታየን ስቃያችንና ፍርሃታችን ብቻ ነው፤ ተስፋ አይታየንም። የተሻለ እውቀት ያለው ኢዮብ እንኳን በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ሆኖ " ሕይወቴ እስትንፋስ እንደሆነ አስብ፤ ዓይኔ መልካም ነገርን ከእንግዲህ ወዲህ አያይም።" (ኢዮብ 7:7) የሞት ዕጣ ከምንጊዜውም ይልቅ ቅርብ የሆነበት ኢዮብ ያለበት ሁኔታ በመከራ የተሞላ ቢሆንም ያ ህይወት ምን ያክል አጭር እንደሆነ በማሰብ አጉረመረመ።

*ሐሙስ ጥቅምት 17* *October 24*

## "ማህ ኤኖሽ?" (ሰው ምንድነው?)

በድጋሚ ራሳችንን በኢዮብ ቦታ ማስቀመጥ ይኖርብናል። እግዚአብሔር በእኔ ላይ ይህን የሚያደርገው

ለምንድነው ወይም ለምንድነው ይህ እንዲመጣብኝ የሚፈቅደው? ኢዮብ ሙሉ ምስሉን አልተመለከተም፤ እንዴት ሊያይ ይችላል?

የሚያውቀው በርሱና በዙሪያው የደረሰውን ነገር ብቻ ነው፤ ለምን እንደሆነም

አላስተዋለም።

**በተመሳሳይ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ የማያውቅ ማን አለ?**

**ኢዮብ 7፡17-21ን ያንብቡ። ኢዮብ በዚህ ቦታ እየገለፀ ያለው ምንድነው? ምን አይነት ጥያቄን ይጠይቃል? የርሱን ሁኔታ ከግምት ውስጥ በማስገባት ጥያቄዎቹ ተገቢ የሆኑት ለምንድነው?**

አንዳንድ የመጽሐፍ ቅዱስ ተመራማሪዎች ኢዮብ ከላይ በተጠቀሰው ጥቅስ ላይ ሲናገር በመዝሙረ ዳዊት 8፡4-6 "ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው? ትጠነቀቅለትስ ዘንድ የሰው ልጅ ምንድነው? ከመላዕክት በጥቂትሾምኸው፤ ሁሉንም ከእግሩ በታች አስገዛህለት።" በሚለው ላይ እያሾፈ ነው ብለው ይሞግታሉ (መዝ. 144፡3-4ን ጨምረው ይመልከቱ) ። ችግሩ ግን የኢዮብ መጽሐፍ የተፃፈው የመዝሙረ ዳዊት መጽሐፍ ከመጻፉ እጅግ ቀደም ብሎ መሆኑ ላይ ነው። ከዚህ አንፃር ስንመለከተው መዝሙረኛው ያንን የፃፈው ለኢዮብ ማጉረምረም እንደ ምላሽ ሊሆን ይችላል።

**በዚያም ሆነ በዚህ "ማህ ኤኖሽ?" (ሰው ምንድነው?) የሚለው ጥያቄ ልንጠይቃቸው ከምንችላቸው ዋና ዋና ጥያቄዎች አንዱ ነው። ማን ነን? እዚህ ያለነው ለምንድነው? የህይወታችን ትርጉምና አላማ ምንድነው? ከኢዮብ ሁኔታ አንጻር እግዚአብሔር የውርጅብኙ ኢላማ (ማዕከል) እንዳደረገው ስላመነ**

**እግዚአብሔር ለምን እንደዚህ እንደሚያስጨንቀው ግራ ገብቶት ነው። እግዚአብሔር እጅግ ትልቅ ነው፤ ፍጥረታቱም እጅግ ብዙ ናቸው፤ ታድያ ከኢዮብ ጋር ምን ጉዳይ አለው? እኛን እያንዳንዳችንንስ ለምን ያስጨንቃል? ዮሐንስ 3፡16ንና 1 ዮሐንስ 3፡1ን ያንብቡ። እነዚህ ጥቅሶች እግዚአብሔር ሰብአዊ ዘርን ለምን እንደሚፈልገው የሚያብራሩት እንዴት ነው?**

---

"ዮሐንስ በጠፊው ሰብአዊ ዘር ላይ አብ ያለውን ፍቅር ርዝመት፣ ጥልቀትና ስፋት ሲመለከት በአግራሞትና

በአክብሮት ተሞላ። ይህንን ፍቅር ለመግለፅ ምቹ ቃላትን አላገኘም፤ ነገር ግን ዓለም ሁሉ እንዲያይ "የእግዚአብሔር ልጆች ተብለን ልንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንደሰጠን እዩ" አለ። ይህ የሰውን ልጆች ዋጋ እንዴት ከፍ አያደርገው! በኃጢአት ምክንያት የሰው ልጆች የሰይጣን ተገዢዎች ሆኑ። ከቁጥር በላይ በሆነው የክርስቶስ መስዋዕትነትና በእርሱ ስም በማመን የአዳም ልጆች የእግዚአብሔር ልጆች ይሆናሉ። የሰውን ስጋ በመልበሱ ክርስቶስ ሰብአዊ ዘርን ከፍ አደረገው።" Ellen G. White, Testimonies for the Church, Vol. 4, P. 563

*አርብ ጥቅምት 18* *October 25*

## *ተጨማሪ ሀሳብ*

"በሳይንስና በምርምር እጅግ በተመጠቀበት በዚህ ዘመን የክርስትናው "የምስራች" ከተአማኒነት እየራቀ፣ የህይወት መሠረትነቱ፣ ለአእምሮ አስፈላጊነቱና አስተማማኝነቱ እየቀረ መጥቷል። ሁሉን ቻይና ዘላለማዊ የሆነው አምላክ በአንድ የታሪክ ወቅትና ቦታ በድንገት ሰው ሆኖ መጥቶ በአሳፋሪ ሁኔታ የመሰቀሉ ሁኔታ ተአማኒነት በሚያሳዝን መልኩ ተሸርሽሯል። ከሁለት ሺህ አመታት በፊት በዩኒቨርስ ውስጥ ደግሞ እጅግ ትንሽ በሆነች ፕላኔት ውስጥ ብዙም ገናና ባልነበረች ጥንታዊት አገር ብዙም የማይስብ ክስተት ዓለምአቀፋዊ ወይም ዘላለማዊ ተፅዕኖ አምጥቷል የሚለው እምነት በምክንያት ለሚያምን ሰው አሳማኝነቱ እየቀነሰ መጥቷል። ዩኒቨርስ ፍላጎት ቢኖረው እንኳን ለዚያች የጥቂት ጊዜ ክስተት ትኩረት ሰጥቶ ይከታተለዋል ማለት ዘበት ነበር። በዚህ ለእያንዳንዱ እምነት ሳይንሳዊ፣ ተግባራዊና ይፋ የሆነ ማረጋገጫ በሚፈለግበት የሰለጠነ ዘመን የክርስትና አስፈላጊነት አጠያያቂ ነው።" Richard Tarnas, Passion of the Western

Mind(New York: Ballantine Books,1991) Pg. 305

**እንደዚህ ብሎ ማሰብ ችግሩ ምንድነው? ይህ ጽሁፍ "ሳይንስና ምክንያት" ስለ እግዚአብሔርና ስለ ፍቅሩ ለመናገር ውሱን ስለመሆናቸው ምን ያስተምረናል? "ሳይንስና ምክንያት" በራሳቸው ሊያገኙት የማይችሉት የተገለጠ እውነት እንደሚያስፈልግ ይህ የሚያሳየን እንዴት ነው?**

## የመወያያ ጥያቄዎች:

1. እንደ ክርስትያን "ሰው ምንድነው?" ለሚለው ጥያቄ ምን መልስ ይሰጣሉ? መልስዎ በእግዚአብሔር ከማያምን ሰው መልስ በምን ሊለይ ይችላል?
2. ኮርማክ ማካርቲ "ከሞት ባሻገር የሙታን ሁኔታን ሲፅፍ "ሞት ህያው የሆነ ሁሉ ተሸክሞት የሚዞረው ነገር ነው።" ከሞት በኋላ ስለሚሆነው ነገር ያለን መረዳት ስለሞቱት ወዳጆቻችን ስናስብ መፅናናትን የሚሰጠን ለምንድነው? ከህይወት ብዙ ችግሮች ነፃ ሆነው በሰላምና በእረፍት መሆናቸውን ስናስብ የተወሰነ መጽናኛ አናገኝ ይሆን?